የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት
ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

ቁጥር/Ref.No: ኢ.ሲ.ማ.ድ.ም/ቤ7 303/15
ቀን/Date ጥቅምት 24/2015 ዓ.ም.

# ከኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ም/ቤት የተሰጠ መግለጫ

**ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ.ም. አዲስ አበባ፡-** በኢፌዲሪ መንግስትና ህወሓት መካከል በአፍሪካ ህብረት አስተባባሪነት የተካሄደው የሰላም ድርድር ፍሬያማ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ለተደረገው ሁሉ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ከፍተኛ ምስጋናውን ይገልጻል።

ተደራዳሪ አካላቶቹ የትጥቅ ግጭቱን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ስምምነት ላይ በመድረሳቸው ምክር ቤቱ እንኳን ደስ አላችሁ እያለ ስምምነቱ በመተግበሩ ረገድ ከፍተኛ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ እንደሆነ በአጽንኦት ያምናል።

ምክር ቤቱ የሰላም ስምምነት አፈፃፀሙን በመከታተል፣ በሰብአዊ ዕርዳታ አቅርቦት፣ በመልሶ ማቋቋም ላይና አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት በማንኛውም ሁኔታ አዎንታዊ ሚናውን ለመጫወት ዝግጁ መሆኑን አበክሮ ይገልጻል።

የሰላም ድርድሩን ላስተባበረው የአፍሪካ ህብረት፣ ተደራዳሪዎቹን ተቀብለው ላስተናገዱት የደቡብ አፍሪካ መንግስት እና ህዝብ፣ የሂደቱን ታዛቢዎች እንዲሁም የሰላም ድርድሩ በስኬት እንዲጠናቀቅ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት በሙሉ ምክር ቤቱ ምስጋናውን ያቀርባል።

***<u>ስለ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት</u>***

*የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ምክር ቤት ሲሆን በኢፌዲሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ተመዝግበው ዕውቅና ያገኙትን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ከ4000 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን አቅፎ በመስራት ላይ ይገኛል።*

(251) 11 853 2005/8/9
Email: ECSOC22@gmail.com
URL:www.ecsoc.net
@ethiopian.cso_council
@Eth_CSO_Council
@ethiopian_cso_council
Ethiopian Civil Society Organizations Council
**Location:** Left flank, 3rd floor, Hibr Building of Hibret Bank, Addis Ababa Ethiopia